April 19, 2002

# ቀስተደመና ሬድዮ
# ትችት
## (ከመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ የስነጽሁፍ ዝግጅት ክፍል የቀረበ)

## ዳግም ግንጠላ

የቅኝ አገዛዝ ዘመን አልቆለታል ተብሎ፣ የህዝቦች መብት ከሁሉም በላይ ከበሬታ የሚሰጠው እሴት ነው ተብሎ አፍሪካ ከባእድ አገዛዝ ነጻ ከወጣች አርባ አመት አለፋት። ባገር ወዳድ መሪዎቹዋና በታጋይ ህዝቦቹዋ ትግል ከመቶ አመታት በፊት አለምን አጥለቅል ቆ የነበረውን የቅኝ አገዛዝ ቀንበር ብቻዋን ተቁዋቁማ ነጻነቱዋንና ክብሩዋን አረጋግጣ የነበ ረችው ኢትዮጵያ ግን ዛሬ ይህ የግፍ አገዛዝ አክትሙዋል በሚባልበት ወቅት አለም ልብ ሳይለው ባስር አመት ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ሞተው በተቀበሩ የቅኝ ግዛት ውሎች፣ ባረጁ ባፈጁ የቅኝ ገዥወች ህዝቦችን የመቃረጥ ዘግናኝ ዘዴዎች አማካኝነት ኢትዮጵያውያን ሳይ ፈቅዱ፣ ሃሳባቸውን ሳይጠየቁ ብቻ ሳይሆን «እናት አገራችን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያ ብቻ ነች» እያሉ እየጮሁ የዜግነት ዝውውር ሰለባ ሆነዋል።

ከተባበሩት መንግስታት ውሳኔዎች፣ ከዩኒቨርሳል የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች! ከአለ ም አቀፍ የውል ህግጋት አንጻር ምንም ተቀባይነት በሌለው ሂደት የዛሬ አስር አመቱ የኤ ርትራ ሬፈራንደም ተብየ የፈጠራቸውን ችግሮች ሳንወጣ አሁን ደግሞ ዘሄግ የተሰየመው የድንበር ሽምግልና ኮሚሽን ሌሎች ኢትዮጵያውያንን ለግዴታ መገንጠል ዳርጉዋቸዋል።

የዛሬ አስር አመት ግድም በነሻብያ የመገንጠል ትግል ያልተሳተፉ፣ ከዚያም አልፈ ው ይህንን ትግል ተቃውመው የተዋደቁ አፋርና ኩናማ ኢትዮጵያውያን ከመቶ አመት በፊ ት የተደረገባችሁ ውል አለና በዚያ መሰረት ከእንግዲህ ኤርትራውያን ናችሁ ተብለው ወን ድም ከወንድሙ፣ እህት ከእህት፣ እናት አባት ከልጅ ዘመድ አዝማድ ተለይቶ በሸአብያና ወያኔ ሰራሽ ወጥመደኛ ድንበር ታጥሮና ተለያይቶ እንዲኖሩ ተፈረደበባቸው።

የተባበሩት መንግስታትም ሆነ የአንድን ህዝብ የሃገር ፍቅር ትኩሳት ባመት ነፍስ ወ ከፍ ገቢ እየለኩ ድሃ ህዝብ አገሩን መውደዱ ሊገባቸው የማይችል ሃያላን የተባበሩት መ ንግስታት ራሱ ከሰላሳ አመት በፊት አንድ ህዝብ በቅኝ ግዛት ተይዙዋል እንዲባል ቅኝ ገ ዥ ከተባለው አገር ከጂኦግራፊ አንጻር የተለየ አገር መሆን አለበት! ቅኝ ይገዛዋል ከተባለ ው አገር በባህልም በቁዋንቁዋም የተለየ መሆን አለበት ብሎ ያጸደቀው ውሳኔ ለኢትዮጵየ አ ሲሆን እንዳይሰራ አድርገዋል። ከዚያ ይልቅ ኩታ ገጠሙዋ ኤርትራ የኢትዮጵየአ የቅኝ ግዛት ተባለች። ከዚያ ይልቅ ከዚህ ወዲህ ያሌው አፋር ከዚህ ወዲያ ያለውን ወንድምህን ! ከዚህ ወዲህ ያለሽው ኩናማ በዚያ በኩል ያለችውን እህትህን፣ ከዚህ በኩል ያለሽው ትግራይ ከወንዝ ማዶ ያለውን ወንድምህን፣ በዚህ በኩል ተከልለህ የነበርከው ሳሆ በዚያ በኩል የተከለችውን እህትህን በቅኝ ግዛት ይዘሃል በሚል ታይቶም ተሰምቶም በማይታወቅ ግፍ ህዝቦች፣ ብሄሮች ቤተሰቦች የግድ እንዲለያዩ ተደረገ።

እነዚህ ህዝቦች ላይ የተፈጸመው ግፍ በዘግናኝነቱ ባለፈው ክፍለዘመን ቅኝ ገጅዎች አፍሪካን ሲቃረጡ ከፈጸሙት ግፍ የባሰ ነው። መጀመሪያ ክፍለዘመኑ መጀመሪያ ላይ አ ንድ የነበሩ ህዝቦች በቅኝ ግዛት ውሎች ተከፈሉ። አምሳ አመት ቆይተው እነዚህ ህዝቦች ኢትዮጵያውያን መንድሞቻቸው ጋር ተደባለቁ። አገራቸው ኢትዮጵያን መልሰው አገኙ። ላምሳ አመታት ያህል በኢትዮጵያዊነታቸው ኮርተው በተለይ አፋሮችን በሚመለከት ባንድ አገር ከመኖር ባሻገር በኢትዮጵያ ክልል ውስጥ የብሄራዊ የግዛት አንድነታችንን ብለው ያካሄዱት ትግል ተሳክቶ ሪጅናል ኦቶኖሚ ተጎናጸፉ። የሻብያ ሬፈራንደም ተብየ ፈሊጥ ደ ግሞ እንደገና ወደ ክፍለዘመኑ መጀመሪያ መልሶ ከፋፈላቸው። የዚህ ትግል ሃያልነትና ጽና ት የሚመጣው ለኢትዮጵያ ካለው ፍቅር ብቻ ሳይሆን በዚህ መልክ አግኝቶ ያጣ ህዝብ የ ሚያካሂደው ትንንቅ እንደሆነ ካልገባን ስለዛሬውም ሆነ ስለመጭው ትግሉ ምንም ግንዛቤ አይኖረንም።

ይህንን ግፍ አልቀበልም ብሎ ሲነሳና ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ ከሽአብያ ጋር ሲዋጋ አሁንም በታሪክ ታይቶም ተሰምቶም በማይታወቅ ሁኔታ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚለው መንግስ ት ከዚህ ህዝብ ደመኛ ጠላት ከሆነው ሃይል አብሮ በስተጀርባም በፊትለፊትም ወጋው። ይህ ጥያቄ ባልተፈታበትና ነገ አገራችን ኢትዮጵያዊ ራእይ ያለው ሌላው ቢቀር የአፋርን ህዝብ የኢትዮጵያዊነት ህልም ከሽአብያ አብሮ የማይዋጋ ምንግስት ስትታደል ሊፋፋምና ድል ሊያደርግ የሚችል ህልምና ትግል ባለበት ሁኔታ አሁን ደግሞ በዚህ የድንበር አካላይ ከመባል ይልቅ የህዝብ ብወዛ ኮሚሽን ሊባል በሚገባው አካል ሌሎች ኢትዮጵያውያን ሳ ይጠይቁም ሳይጠየቁም ብቻ ሳይሆን ተቃውሞ እያሰሙ ከዛሬ ከሚያዝያ 5 ቀን 1994 ኢ. ም. ጀምሮ ኢትዮጵያዊነታችሁ ተሰርዞ ኤርትራዊ ሆናችሁዋል ተብለዋል። ያለፈው የህዝቦ ች ብወዛ ሂደት ያነሳቸው ጥያቄዎች እንኩዋን ሊፈቱ ቀርቶ የመፋፋማቸው አደጋ እያንዣ በበ ባለበት ወቅት ለኢትዮጵያም ክብርና ጥቅም ለኤርትራም ሰላምና መረጋጋት አደገኛ የ ሆነ የዳግም ግንጠላ ሂደት ተከስቱዋል።

ከወዲሁ የተነሳባቸው መንደርደሪያዎች ሁሉ የተሳሳቱ ስለሆኑ ቤት ዘግቶ ወረቀት ላ ይ ካርታ እየሳለ ህዝቦችን እበውዛለሁ ከሚልው ከዚህ ኮሚሽን ማንም ቢሆን ለኢትዮጵያ ም ሆነ ለኤርትራ ህዝቦች ሰላምና ወንድምማችነት፣ ለነዚህ ህዝቦች ልማትና ብልጽግና የ ሚያረጋግጥ ውሳኔ አይጠብቅም ነበር። አለም አቀፍ ኮሙኒቲ የተባለው ነገር ኤርትራን የ ኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት አድርጎ ከሚቆጥር መንደርደሪያ እስከተነሳ ድረስ ያሉትን ድንበሮች እንዳለ ቢተውም የቀድሞው የመገንጠል ሂደት የፈጠራቸውን ችግሮች ስለማይፈታ፣ ያሉ ትን ድንበሮች አሸጋሽጋለሁ ቢል ደግሞ «የቅኝ ግዛት ውሎች» በተባሉት ሰነዶች እንኩዋ ን ተከፍለው የማያውቁ ቤተሰቦችን በአለም አቀፋዊ ድንበር አካልላለሁ በማለት በዳግም ግንጠላ ሂደት ቢሰማራ ደግሞ በነባር ችግሮች ላይ በአናት በአናት ሌሎች ተጨማሪ ችግ ሮች ስለሚፈጥር ይህ ኮሚሽን ከወዲሁ ለውድቀት የተዳረገ አካል እንደነበረ ግልጽ ነው።

በዚህ ጸረ ህዝብና ግፈኛ ውሳኔ ምክንያት በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰራዊቱን ጨምሮ የ አገዛዙን መከፈል በማስከተል በኢትዮጵያ ውስጥ የእርስበርስ ግጭት የሚፈጥርበትና የሽአ ብያ ጦር ወገን ለይቶ ጣልቃ በመግባት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚፈጠረውን ግጭት የሚያባ ብስበት አስጊ ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ይፍጠንም ይዘግይም እነዚህ ወገኖቻችን በግድና በ አለም አቀፍ ውሳኔ ኤርትራዊ መባላቸውም ቢሆን በኤርትራ ይበልጥ አለመረጋጋትን ይፈጥ ር እንደሆን እንጂ ሰላም፣ ብልጽግናን፣ መረጋጋትን አያመጣም።

የኢትዮጵያም ሆነ የኤርትራ ህዝቦች ከአለም አቀፍ ኮሙኒቲ ተብየው ነገር ምንም መጠበቅ የለባቸውም። ከወያኔና ሽአብያም ቢሆን ጦርነት፣ አፈና፣ ድህነት፣ ጉስቁልና እ ንጂ ምንም ፋይዳ ያለው ነገር መጠበቅ እንደማይቻል ያለፉት አመታት ሂደቶች አስተምረ ዋቸዋል። ዴሞክራሲ፣ ፍትህ፣ ወንድማማችነት፣ እድገት የሚባሉት የጋራ አላማዎቻችን ከ ባድ ቁምነገሮች ስለሆኑ ለነዚህ ሁለት አጥፊ ሃይሎች የሚተው አይደሉም። ችግሮቻችንን ተወያይተን በወንድማማችነትና በመከባበር መንፈስ ለመፍታት የኤርትራና የኢትዮጵያ ዴሞ ክራቶች ተገናኝተን የመወያያው ጊዜ ደርሱዋል እንላለን።

የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን የስነጽሁፍ ዝግጅት ክፍል)

ሚያዝያ 11 ቀን 1994 ኢ.ም.